# ግልፅ ደብዳቤ ለፕሮፎሴር መስፍን ወልደማርያም ከይልማ በጋሻዉ

ሰላም ጋሼ መስፍን፤ ስንቱ እልፍ አዕላፍ ወገን በተከተታይ አረመኔዎች እጅ በረገፈበት ዘመነ ኩነኔ አንተንም (አስተማሪያችን) እኛንም ጥቂት የተረፍን የተማሪ እንቅስቃሴ ሰለባዎችን በሕይወት ለዛሬ ላደረሰን አምላካችን ታላቅ ምስጋና ይግባዉ። ኑሮ ታሉት መቃብር ይሞቃል ለማለት እንጂ ለነገሩ በቁማችንም አለን አልሞትንም ለማለት ኢይደለም። ስንት ንፅሓን ወገኖቻችን ተሰዉተዉ ዉድ አገራችን ከባድ ጣጣ ላይ ወድቃ በምትገኝበት በዛሬዉ እጅግ አሰቃቂ ዘመን ሁሉም ሃቀኛ ዜጋ እዉነቱን መመስከር ይጠበቅበታል። በተለይ እንዳንተ ያሉት የዕድሜ ባለፀጋዎች ላዲሱ ትዉልድ ትክክለኛዉን ታሪክ አስጨብጠዉ ማለፍ ይገባቸዋል። ይህቺን አጭር ደብዳቤ እንድጽፍልህ የገፋፋኝ በቅርቡ ለኢሣት ቴለቪዝን ቃለመጠይቅ የሰጠሃቸዉ አንዳንድ መልሶች እጅግ በጣም ስላሳዘኑኝ ጥቂት ሃቆች ለማስጨበጥ ያህል ነዉ።

በነገራችን ላይ አንባቢ እንዲረዳልኝ የምፈልገዉ እኔ የዩኒቬርሲቲ ተማሪ በነበርኩበት ወቅት እርሱ ደግሞ መምህር ነበር። በዚያን ወቅት የነበረዉ ጥሩ ባህልና መቀራረብ አንተ አንተ መባባልን ይጨምር ስለነበር አንተ ብዬ በመጻፌ ንቀት እንዳይመስላችሁ ላሳስብ እወዳለሁኝ።

፩ኛ/ ‘የ1953 ዓ/ም የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ ምንም ለዉጥ አላመጣም፤ ምንም ምሣሌም አልጣለም’ ብለህል።እረስተሄዉ እንደሆነ እንጂ ሃቁ ግን እንደሚከተለዉ ነዉ።

ሀ) የመፈንቅለ መንግሥቱ መሪ ጄ/ መንግሥቱ ነዋይ ነበረ። እርሱም የቀ/ኃ/ሥ ክብር ዘበኛ ዋና አዛጅ እንደመሆኑ መጠን በግሉ ሁሉም ነገር የተሟላለት ሰዉ እንጂ ምንም ያልጎደለበት እጅግ ከፍተኛ መኮንን የግሉን ጥቅም ጥሎ መስዋእትነት የከፈለዉ በወቅቱ በኢትዮጵያ ዉስጥ በነበረዉ ግፍና ጭቆና ምክንያት ነበር።

ለ) ታናሽ ወንድሙ ገርማሜ ነዋይ ደግሞ አሜሪካ በትምህርት ላይ በነበረበት ጊዜ እነጆን ኤፍ ኬነዲና ከዋሚ ኒክሩማህ የመሳሰሉ የዲሞክራሲና የእኩልነት ትግል አቀንቃኞች ባልደረባ ነበረ።

ሐ) ሌሎቹ ደግሞ እነወርቅነህ ገበየሁን የመሳሰሉ ታላቅ ራዕይ የነበራቸዉ የሥር ነቀል ትግል አንቀሳቃሾች ነበሩበት።

መ) በወቅቱ የተደረገዉ የመፈንቅለ መንግሥት ሙከራ በተለያዩ ዉስጣዊና ዉጪያዊ ምክንያቶች ሊከሽፍ በቃ (ለዚህ ብዙ መረጃዎች ስላሉ ጠይቆ መረዳት ይቻላል)።

ሠ) የመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ ለጊዜዎ ቢከሸፍም ታላቅ ምሣሌ ጥሎ ስለከማለፉ ጨርሶ መካድ አይቻልም። ከዚያ በመቀጠል በ1960ዎችና 70ዎች እንደ እሳተ ገሞራ የተቀጣጠለዉና በዓለም ስመጥር የነበረዉ የተማሪዎች እንቅስቃሴ የተፋፋመዉ ከመፈንቅለ መንግሥቱ ሙከራ በመቀጠል ነበር።

፪ኛ/ **'በቀ/ኃ/ሥ ዙፋናዊ አገዛዝ ዘመን ተማሪዎች የተንቀሳቀሱት ለሥልጣን ፍለጋ ነበር፤ በንጉሱ አልጋ ላይ ሊወጡ ያደረጉት አጉል መንጠራራት ነበር'፤ ወደፊት አይወጣም እንጂ የእንቅስቃሴዉ መሪ እሼቱ ጫሌ ነበር፤ ወዘተ' ብለሃል።**

ይሄም አባባል ደግሞ ከሃቁ እጅግ የራቀ ነዉ። ለምን ብትለኝ፤

ሀ) አንተና አለማየሁ ልበል አንድ የዩኒቬርሲቲ የአማርኛ መምህር በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ላይ እየጻፋችሁ የተማሪዉን እንቅስቃሴ ያኔም ትኮንኑ ነበር። የጠራ አቋምም አታሳዩም ነበር።

ለ) ተማሪዉ የታገለዉ የፍጹም ባላባታዊ አገዛዝ ተወግዶ የዲሞክራሲ ሥርዓት ተመስርቶ መሬት ላራሹ እንዲሆን፤ ብሄሮች ሁሉ እኩል እንዲሆኑና ለብሄራዊ ብልፅግና ሕዝብን ለማነሳሳትና ለማንቃት እንጂ ተማሪዉ ዝም ብሎ አንተ እንዳልከዉ ዘሎ ሥልጣን ላይ ሊፈናጠጥ እንዳልነበረ የዚያ ዘመን ስመጥር ታሪክ ለራሱ የሚናገር ሃቅ ነዉ። እኔም ባቅሜ እዚያዉ ትግል ዉስጥ የነበርኩ ስለሆንኩ ያልሆንኩትን ስትነግረኝ እጅግ በጣም ከፍቶኝ ነዉ።

**፫ኛ/ የመርማሪ ኮሚሽንን ሚና በተመለከተ አሁንም ገና በደንብ ያልተመለሱ ጥያቄዎች አሉ።**

ሀ) አንተ እንዳልከዉ የተቋቋማችሁት በነፃ ካቢኔት ሳይሆን በደርግ ዉሳኔና ተፅእኖ ሥር ነበር።

ለ) 'እኛ ጥናታችንን ጨርሰናል፤ ካሁን ወዲያ ጠብ መንጃዉ በናንተ እጅ ስለሆነ እኛን ተዉን' ብላችሁ ለመንግሥቱ/ለደርግ አዳሳሰባችሁ ተወርቶ ነበር። ይሄን ጥያቄ በተለመከተ እስካሁን አንዳችሁም በይ አላመናችሁ ወይ አላስተባበላችሁም። ሀቁን ብትነግረን እግዚአብሄር ይወደዋል። ምክንያቱም የናንተን ጥናት ተከትሎ ስንት መተኪያ የማይገኝላቸዉ ዕፁብ ድንቅ የነበሩ አባቶች ለፍርድ እንኳን ሳይቀርቡ በፋሺስት አረመኔ ደርግ እጅ የተረሸኑት።

ዉድ ጋሼ መስፍን፤

ባሁኑ ደረጃ ከንፁሓን አባቶችና እናቶች የሚጠበቀዉ አዲስ ፓርቲ መመስረትና ወደወያኔ መጠጋት ሳይሆን በገለልተኛነት ቆመዉ የተለያዩትን ተቃዋሚ የፖሊቲካ ድርጅቶች ማቀራረብና ማሳተፍ ነበር። በ2003 ዓ/ም የህብረት ምሥረታ ላይ ብፁአን አባቶች የተጫወቱት ሚና ልክ ይሄን ነበር የተመለከተዉ።

ሆኖም ግን ይህቺን ቃሌን እንደድፍረት አትዉሰድብኝ። ያለፈዉ አለፈ። ብዙ ተጽዕኖዎች ሊኖሩ ይችላሉ። አሁን ግን አንድ እግራችን መቃብር ላይ በተተከለበት ወቅት ላዲሱ ትዉልድ ሃቁን አስጨብጠን ብናልፍ ለወገን ይበጃል፤ ነፍሳችንም በሰማይ ይማራል የሚል ግምት ስላለኝ ነዉ።

የእዉነት አምላክ ቸሩ እግዚአብሔር አገራችንን ይጠብቅልን፤ አሜን።